Cambridge
Public Health
Department

ፌብሩዋሪ 4፣ 2020

ዉድ የ CPS ቤተሰቦች፣

ለኬምብሪጅ የህዝብ ትምህርት ቤቶች (CPS) ማህበረሰብ ስለ 2019ኙ የኮሮና ኖቬል ቫይረስ ተጨማሪ መረጃ ጋር እንፅፍላችኋለን። ይህ አዲስ የአተነፋፈስ (ሳምባ) ቫይረስ በመጀመሪያ የታየዉ በዉሃን፣ ቻይና በዲሴምበር ነበር። በፌብሩዋሪ 1፣ በማሳቹሴትስ የመጀመሪያዉ የኖቬል ኮሮና ቫይረስ በቦስተን ነዋሪ በሆኑ ሰው ላይ መገኘቱ ተረጋገጠ። እኚህ ግለሰብ አሁን በማግለያ ዉስጥ ይገኛሉ።

ይህ ዜና **አደጋዉ በማሳቹሴትስና በአሜሪካ ዉስጥ ለሚኖሩ ሰዎች አነስተኛ በመሆኑ** የስቴትና ፌዴራል የጤና ባለሙያዎችን ግምገማ አይለዉጠዉም። አደጋዉ አነስተኛ ስለሆነ፣ የማሳቹሴትስ የጤና ባለሙያዎች የትምህርት ቤት ዝግጅቶችን ጨምሮ፣ የቡድን እንቅስቃሴዎች እንዲሰረዙ አይመከሩም።

ይህ እያደገ የመጣ ሁኔታ ነዉና፣ የአካባቢ፣ የስቴት፣ እና የፌደራል የጤና መምሪያዎች ወኪሎች ወረርሽኙን በቅርበት እየተከታተሉት ነዉ። የቅርብ ጊዜ መረጃ በእዚህ ይገኛል፡

- ስለ 2019 Novel Coronavirus (ኖቬል ኮሮና ቫይረስ) (Centers for Disease Control and Prevention (የበሽታና የመከላከያ ማዕከሎች))፦ https://www.cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/
- ህብረተሰቡ ማድረግ የሚገባው (CDC)፦ https://www.cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/about/what-you-should-do.html
- ለመንገደኞች መረጃ (CDC)፦ https://www.cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/travelers/index.html
- 2019 ኖቬል ኮሮና ቫይረስ (የማሳቹሴትስ ጤና መምሪያ)፦ https://www.mass.gov/2019coronavirus

**ማድረግ የሚችሉት**

በማሳቹሴትስ ከፍተኛ የጉንፋን (ኢንፍሉኤንዛ) ወቅት ስለሆነና የጉንፋንና ሌሎች የአተነፋፈስ በሽታዎችን መስፋፋት ለመከላከል የCPS ቤተሰቦች በሚከተሉት ያግዛሉ፡

- የቤተሰብ አባላት የጉንፋን ክትባት እንዲወስዱ ማበረታታት።
- ሳሎችንና ማስነጠሶችን መሸፈን።
- እጆችን በሳሙናና ዉሃ ብዙ ጊዜ መታጠብ። ሳሙናና ዉሃ ከሌለ፣ ቢያንስ 60% አልኮሆል ያለዉ እጅ ማፅጃ ይጠቀሙ።
- ልጆች በታመሙ ግዜ በቤት እንዲቀሩ።

ጥያቄዎች ወይም ጉዳዮች ካልዎት፣ እባክዎን በስልክ ቁጥር 617-983-6800 የማሳቹሴትስ ጤና መምሪያን ያናግሩ።

Claude A. Jacob, MPH
የጤና መምሪያ ዋና ባለሙያ
ኬምብሪጅ ሄልዝ አላያንስ
የኬምብሪጅ ከተማ

Lisa Dobberteen, MD, FAAP
የት/ቤት ጤንነትና የጤና መርሃግብሮች
የሕክምና ዳይሬክተር
የኬምብሪጅ ጤና መምሪያ

Tracy Rose-Tynes, MS, BSN, RN
የት/ቤት ጤና አገልግሎቶች ነርስ
አስተዳዳሪ
የኬምብሪጅ ጤና መምሪያ

119 Windsor Street
Cambridge, MA 02139
Phone: 617.665.3800 | Fax: 617.665.3888
www.cambridgepublichealth.org

CHA Cambridge Health Alliance